# የላንግስተን ሂውዝ ግጥሞች

ትርጉም

በ

አምሀ አስፋው

**የደራሲው መብት በህግ የተጠበቀ ነው።**

Copyright © 1996  Amha Asfaw

Copyright © 1994 by the Estate of Langston Hughes.
Reprinted by permission of
Harold Ober Associates Incorporated

**የፊት ሽፋን - ሶስና ቀይ ስትለብስ**
**የጀርባ ሽፋን - ላንግስተን ሂውዝ**

ለአባቴ

ለደጃዝማች አስፋው ገብረ አማኑኤል፡፡

# ማውጫ


| | |
|---|---|
| ኔግሮ ስለወንዞች ይናገራል | 19 |
| የስርግ ጎዳና ትርምስ | 20 |
| ድምር | 20 |
| ወንድማማች | 21 |
| ሀርለም | 21 |
| ጉራማይሌ ዘፈን | 22 |
| ጦር ሳይከተት | 23 |
| የጃጀ የከፋ ትናንት | 24 |
| ክትመት | 24 |
| ወገኖቼ | 25 |
| ደንቃራ | 25 |
| ስሞታ | 26 |
| አንጎላ የጥያቄ ምልክት | 26 |
| ስለመኖሪያ ቤት ትንሽ እንጉርጉሮ | 27 |
| የሉሙምባ መቃብር | 28 |
| ጃይሜ | 29 |
| ጭቆና | 29 |
| አፄ ሀይለስላሴ | 30 |
| አቃቤ ተስፋ | 30 |
| እባክዎ ይግለፁልኝ | 31 |
| ወደባህር መልስ | 31 |
| ጉልላት | 32 |
| የመንግስት ማስታወቂያ | 32 |
| አዲስ ልብስ | 33 |
| ጅል እንሰሶች | 33 |
| እንቆቅልሽ | 34 |
| ተስፋ | 34 |
| ፀሎት፣ ለክረምት ሌሊት | 35 |
| የሰፈር ስብሰባ | 35 |
| ይዘት | 36 |
| የአሜሪካ ሰቀቀን | 36 |
| የፅጌረዳ መአዛ | 37 |
| የራስን ህይወት ለማጥፋት ኑዛዜ | 37 |

| | |
|---|---|
| የሁለት ሌቦች ቅንቅን | 38 |
| ነፃነት - ፩ | 39 |
| የምኞት አይነት | 40 |
| የባህር ፀጥታ | 40 |
| ፍርሀት | 41 |
| የቾገራት ሴትዮ | 41 |
| ልጅነት | 42 |
| የሜዳ አበባ | 42 |
| የምድር ዜማ | 43 |
| ፀሎት | 43 |
| የተስፋ ቡጊ | 44 |
| ለማኝ ልጅ | 45 |
| ግድግዳዎች | 45 |
| ለአንዳንድ ምሁራን | 46 |
| ጥያቄ | 46 |
| የመፀው ግጥም | 47 |
| የመጋቢት ጨረቃ | 47 |
| አርዴላ | 48 |
| የበሽተኛ ክፍል | 48 |
| የማለዳ መንገደኞች | 49 |
| ዘዴዎች | 49 |
| ሶስና ቀይ ስትለብስ | 50 |
| የክርስቲያን አገር | 50 |
| እንጉርጉሮ | 51 |
| ምክር | 51 |
| ጊዜያዊ ፍቅር | 52 |
| ድካም | 52 |
| ይሻላል | 53 |
| አዲስ ጨረቃ | 53 |
| ታሪክ | 54 |
| የኢትዮጵያ ጥሪ | 54 |
| ፍትህ | 55 |
| መንግስተ ሰማያት | 55 |
| ሀምራዊ ምኞት | 56 |
| መሹለኪያዎች | 56 |

የግል 57
እንደ ነፃነት ያሉ ቃሎች 57
አረንጉዋዴ ትዝታ 58
ሀዘን 58
ስልቾታ 59
ትካቴ 59
ያገር ናፍቆት ትዝታ 60
የካራቢያን ፀሀይ ጥልቀት 60
ኩ ክላክስ 61
የመጨረሻው ኩርባ 62
ጨቅላ 62
ማማ 62
እኔና ዝማሬዩ 63
ነፃነት - ፪ 64
አስረዱኝ 64
ጥቁር ሰራተኞች 65
እግዜር 65
ቀለም 66
ደሴት 66
ፍፃሜ 67
ሰላም 67
ርኩስ 68
ወጣት መርከበኛ 68
ማደሪያ ቤት 69
ወጣት ሸርሙጣ 69
የአፍሪቃ-አሜሪካዊ ስባሪ 70
ዱር አዳሪ 71
ባዶ ቤት 71

# መግቢያ

## <u>ስራ</u>

ስራ እንዴት ነው?

ምን ለውጥ አለው፤
ነው እንደጥንቱ፣
ነው እንደድሮው፤
አንዴ ከሆንክ ባርያ፣
ዘለአለም ባርነት ነው።

ከቻላችሁ፣ አትገዙ ለገንዘብ፣
ከረጅም የምቾት ባርነት፣
ይሻላልና ጉስቁልና፣
በነፃነት።

ስለነገ ሳያስቡ፣
የሚወዱትን እየሰሩ፣
እንደ ላንግስተን ሂውዝ፣
ለዛሬ ብቻ መኖሩ፣
ምንኛ መታደል ነው፣
የገንዘብን እትብት መቁረጡ፣
ለዛሬ ብቻ መጨነቅ፣
የባርነትን ገመድ መበጠሱ።

ምንኛ መታደል ነው፣
ዛሬን ብቻ ማሰቡ፣
የነፃ ህሊና ባለቤት መሆን፣
እንደ ላንግስተን ሂውዝ ሁሉ፤
ምንኛ መታደል ነው።

ላንግስተን ሂውዝ የተባለው ጥቁር አሜሪካዊ ገጣሚ፣ በ 1902 አ.እ ሚዙሪ በሚባል የአሜሪካ ክፍለ ሀገር፣ ጆፕሊን በምትባል ከተማ ተወለደ። አስተዳደጉም ከእናቱና ከሴት አያቱ ጋር በድህነት ነበር። ደግነቱ ለላንግስተን ሂውዝ ገንዘብ ማካበት የህይወቱ ዋናው ተልእኮ አልነበረምና፣ ድህነት ተልእኮውን ለማምዋላት መሳሪያ እንጅ እንቅፋት አልሆነበትም።

እንደ ላንግስተን ሂውዝ ያሉ ሰወች ያስቀኑኛል። ስለነገ አያስቡም፤ የሚኖሩት ለዛሬ ብቻ ነው። እንዲያም ሆኖ ለባርነት አይጋለጡም፤ አይሸጡም አይገዙምና።

ላንግስተን ሂውዝ ስለ ገንዘብ የነበረውን አስተሳብ የሚያሳይ ስለመሰለኝ፣ አንድ ሴት ወይዘሮ በሀብታቸው ተመክተው፣ ተፅእኖ ሊያሳድሩበት ስለሞከሩ የፃፈላቸውን ግጥም አስከትየዋለሁ።

## <u>ገጣሚ ለደጉዋሚ</u>

ማን፣ ምን ሀይል አለው፣
        የሚነግርበት ለኔ፣
እንዲሸጥ፣
        እንዲመነዘር ልቤ?

ቢኖርብኝም መብላት እንጀራ፣
መሸጥ አለብኝ እራሴን፣ ለርሶ፣
        ልቤ እንዳይቆም፣ እንዲመታ?

ምን ግጥም ፃፍክ ዛሬ? ከሚለኝ፣
        የተርከፈከፈበት ወረቀት ሽቱ፣
ከፋብሪካ መስራቱ፣
የማይረባ ሳምንታዊ ደሞዝ ማግኘቱ፣
በስንት ጣእሙ፣
ኧረ በስንት ጣእሙ።

ላንግስተን ሂውዝ በኖረበት ዘመን፣ ሰው እንደነጭ ከልተናገረ፣ እንደነጭ ካልፃፈ፣ እንደነጭ ካላሰበ፣ ደንቆሮነቱን የሚጠራጠር አልነበረም፡፡ እሱ ግን የሚገጥመው እንደወገኖቹ፣ የሚፅፈውም ለወገኖቹ ሲል ነበር፡፡ አፃፃፉ የኒውዮርክን ከተሜወች የአነጋገርና የዘፈን ፈሊጥ የተከተለ በመሆኑ፣ ግጥሞቹን ወደ አማርኛ መመለስ እጅግ ከባድ ነው፡፡ ግን፣ ኢትየጵያን በችግርዋም ጊዜ ሆነ በደስታዋ በግጥሞቹ ያልረሳት ሰው ስለነበረ፣ ኢትየጵያውያን ስሙንና ስራውን ማወቅ ይገባናል፡፡

ላንግሰተን ሂውዝ በ 1966 ኢ.እ ኢትዮጵያን ጎብኝቶ ነበር፡፡ ቀዳማዊ ሀይለ ስላሴም ተቀብለው አነጋግረውታል፡፡ ሰሞኑ የኢትዮጵያ የነፃነት በአል የሚከበርበት ስለነበር፣ በዚያ ሳብያ «አፄ ሀይለስላሴ» የሚለውን ግጥም ፃፈላቸው፡፡

ኢትዮጵያን በብዙ ግጥሞቹ ያነሳታል፡፡ የደጃዝማች ሀይለስላሴ ጉግሳን ከሀዲነት እንኩዋን የሚጠቅስ ግጥም ፅፍዋል፡፡ ከነዚህ ሁለቱ፣ «የኢትዮጵያ ጥሪ» እና «አፄ ሀይለስላሴ» የተባሉት ግጥሞች በዚህ መፅሀፍ ውስጥ ይገኛሉ፡፡

ላንግስተን ሂውዝ ከሰላሳ የሚበልጡ፣ የግጥም፣ የታሪክና የቀልድ መፅሀፎችን ደርስዋል፡፡ ብሮድ-ዌ በመባል የታወቀው የኒውዮርክ ትያትር መታያ ሰፈር ለተመልካች የቀረቡ ድራማዎችንም አዘጋጅትዋል፡፡ በተለይም ጃዝ የሚባለውን የጥቁር አሜሪካኖችን ሙዚቃ ይወድ ስለነበር፣ አያሌ ዘፈኖች የርሱን ግጥሞች ተመርኩዘው ተዘፍነዋል፡፡ ጃዝ የመውደዱን ጉዳይ ካነሳነው፣ አንዴ የኮሚኒስት ማህበር አባል ለምን እንዳልሆነ ተጠይቆ፣ «ጃዝ ስለምወድ ነው፡፡» የሚል መልስ ሰጥትዋል፡፡ ጃዝ፣ በኮሚኒስቶች የተኮነነ ያሞዛዘቅ ስልት ነበርና፡፡

በመጨረሻው ግን፣
    ግጥሞቹም ሆኑ፣ የሉዊ አርምስትሮንግ ትዝታ፣
የወገኖቹ ፍቅር፣
    የሀርለም ኮረዶች እስክስታ፣
ሊያሳልፉለት አልቻሉም፣
    ያን የህይወት ማክተሚያ፣ ፅዋ፡፡

ከኢትዮጵያ በተመለሰ ባመቱ በ 1967 አ.እ በድንገት ታሞ ከዚህ አለም በሞት ተለዩ፡፡

ላንግስተን ሂውዝ የራሱን ታሪክ በሁለት መፅሀፎች ተርኮ ታልና አንባቢውን እዚህ ከማድከም ይልቅ ወደነሱ መምራቱ የተሻለ ይመስለኛል፡፡ አፃፃፉ ውብ ስለሆነ እንደ ጥሩ ልቦለድ እየጣሙ ይነበባሉ፡፡ በሚከተሉት ገፆች ከነዚህ ሁለት መፅሀፎች የምወዳቸውን ክፍሎች አለፍ አለፍ እያልኩ ልተርጉምላችሁ፡፡ ፍላጎቴ፣ ጊዜ ያገኘ ኢትዮጵያዊ «ሰፊው ባህር - The Big Sea» እና «እየተደነቅሁ እንከራተታለሁ - I wander as I wonder» የተባሉትን የራስ-ታሪኮች ወደ አማርኛ እንዲመልሳቸው ለመገፋፋት ነው፡፡

□□□

ባባቱ አስገዳጅነት ኮሎምቢያ የተባለ፣ የታወቀ የኒውዮርክ ገዳመ-ጥበብ ገብቶ ነበር፡፡ ሁዋላ ግን ትምህርቱ እጅ እጅ ስላለው፣ አቋዋርጦ ወደ አፍሪቃ የሚጉዋዝ የንግድ መርከብ ላይ ምግብ አቅራቢ ሆኖ ተቀጠረ፡፡ የሚከተለውን ሲፅፍ አፍሪቃን ለመጀመሪያ ጊዜ ነበር የረገጠው፡፡

> *በነጋታው ዳካርን ጥለን የአፍሪቃን ዳር ተከትለን ወደ ደቡብ መጉዋዝ ጀመርን፡፡ ምድሩ አፍሪቃን መምሰል ጀመረ፣ ያለምክዋት ውብ አፍሪቃ፡፡ ሰው ጥቁር ያማረ፣ ዘንባባው ረጅም የመጠቀ፣ ፀሀዩ ብሩህ የደመቀ፣ ወንዞቹ ጥልቅ የኮሩ፣ ታላቅዋ አፍሪቃ፣ የልቤ የህልሜ አፍሪቃ!*
>
> *የሚያሳዝነኝ ጉዳይ ቢኖር አፍሪቃውያን ጥቁር መሆኔን አለማመናቸው ነበር፡፡ ነገሩ እውነት ነበራቸው፡፡ አያቶቼ*

*ከተለያዩ ዘር ስለመጡ፣ ጥቁርም ሆኜ ጥቁር አልነበርኩም፡፡ እዚህ፣ አሜሪካ፣ አንድም ጠብታ ብትሆን የኔግሮ ደም ያለበት ኔግሮ ተብሎ ይጠራል፡፡ ከአፍሪቃ ግን ቃሉ ራሱ የጠራ ነው፡፡ ጥቁርነት ያልተዳቀለ ንፁህ ውበት ነውና፡፡*

□□□

በ 1924 አ.እ በፓሪስ የሆቴል ቤት አሳላፊ በመሆን ተቀጥሮ ይሰራ ነበር፡፡ እዚያም እንዳለ ሜሪ የምትባል አንድ የሀብታም ልጅ ወደደ፡፡ የሜሪ አባት ለንደንና ሌጎስ የሚመላለስ አፍሪቃዊ ነጋዴ ሲሆን፣ እናትዋ ግን ነጭ እንግሊዛዊት ሳትሆን አልቀረችም፡፡ አባትዋ፣ ሜሪ አንድ እንግሊዛዊ የጦር መኮንን እንድታገባ ቃል ገብቶ ነበርና፣ ከላንገስተን ሂውዝ ጋር መማገጥዋን አልወደደውም፡፡ ስለዚህ በለንደን የታወቀ አንድ ጥቁር ሀኪም፣ ያባትዋ ጉዋደኛ፣ ባስቸኩዋይ ይዝዋት እንዲመለስ ተልኮ ፓሪስ መጣ፡፡ ላንግስተን ሂውዝ ያንን ቀን እንዴት እንዳሳለፈው ሲፅፍ እንዲህ ይላል፡-

*የዚያን ለት እኔና ሜሪ ከላቲን ሰፈር ርቀን ራታችንን ለመብላት ወሰንን - ሀኪሙ ፈልጎ እንዳያገኘን ስንል፡፡ የሞማትር (Montmartre) ከረብታ ጫፍ ሳክሬ-ከር (Sacre-Cœur) ለመድረስ ምንም ያህል ያልቀራት ከ ፕላስ ዱ ቴርትር (place du Tertre) የምትገኝ አንድ ትንሽ ምግብ ቤት ነበር የሄደነው፡፡ ወይን፣ ኤፓል ደ ቮ (èpaule de veau) ሳላድ ደ ሴዞን (Salad de Saison) እና ከር ኣ ላ ክሪም (Cœur à la crème) አዘዝን፡፡ ራታችንን በላንና ጥምልምሉን መንገድ ተከትለን ኮረብታውን በእግራችን ወረድን፡፡ ከዚያም የክሊሽን አውራጎዳና አቋዋርጠን እንዴት እንደሆነ እንጃ፣ ብቻ ራሳችንን ከኔ ቤት ደጃፍ አገኘነው፡፡ ያን ቀጥ ያለ ቅዝቃዜና ጭለማ የወረረውን ደረጃ ተያይዘን ወጣንና ከጣራው ስር የምትገኘው የኔ ክፍል ደረስን፡፡*

*ወደቤት ስንመጣ፣ ከአንድ ሱቅ መስኮት የሜዳ እንጆሪዎች ክምር አይተን፣ እነዚህ የፈረንሳይ ፍሬሴስ ደ ቡዋ (fraises de bois) የሚባሉትን እንጆሪዎችና ሁለት ትናንሽ ጠርሙሶች ብጫ ክሬም ገዝተን ነበር፡፡ የክፍሌ መስኮት ሲከፈት ሰፊ የድንጋይ ደፍ ነበረውና፣ ከዚያ ላይ ተቀምጠን፣ የፓሪስን የጭስ*

*መውጫዎች እያዩን፣ እንጆሪያችንን በክሬሙ እያጠቀስን መጎራረስ ጀመርን፡፡ የፓሪስ ፀሀይ ስትጠልቅም በሀዘን ተመለከትን፡፡ አለመጠን ከፋን፣ ልጅነታችንና አቅመ ቢስነታችንም ተሰማን - የምንፈልገውን ማድረግ አልቻልንምና፣ ስለአባቶቻችንም ሆነ ስለ ገንዘብ ሳንጨነቅ አብረን መደሰት አልሆነልንምና፣ ሆድ ባሰን፡፡*

*የፓሪስ ጣርያ እንደቀይ ናስ ሲያበራ፣ ፀሀይዋ ትልቅ የ ወርቅ ሉል መሰለች፡፡ ቀዝቃዛው የምሽት ነፋስ ፓሪስን ከሚያካብቡት ሜዳዎች መንፈስ ጀመረ፡፡ ሀኪሙም፣ ሜሪ ብዙ ካስጠበቀችው እንደሚቆጣ (አሜሪካ ያብዳል ነው የምንለው) ታወቀን፡፡ ስለዚህ አንድ ጥቁር ኮት የለበሰ ጨምዳዳ ሽማግሌ የሚነዳው አሮጌ ጋሪ አገኘንና ሴንን* (Seine) *አቋዋርጦ ኦዲዮንን* (Odeon) *አልፎ፣ መናፈሻወቹን ሁሉ ዘልቆ ሜሪ ቤት እንዲያደርሰን ተከራዩን፡፡*

*ፀሀይ ስትጠልቅ፣ ተቃቅፈን፣ በዝምታ ተውጠን፣ ፓሪስን በጋሪ ማቋዋረጥ ጀመርን፡፡ የመጀመሪያወቹ ከዋክብት ማንፀባረቅ፣ ቀደም ብለው የተለኮሱት የ ሴኑ* (Seine) *መብራቶች መታዬት፣ አዲስ የበቀሉት ለምለም ቅጠሎች ደሞ ልዝብ ኮሽታቸውን ማሰማት ጀመሩ፡፡ በቅዱስ ዠርሜን ጎዳና ስንጉዋዝ አካባቢያችን በ መኪና ጥሩምባና በአውቶቢስ እርምራሞ የተዋጠ ነበር፡፡ ለኛ ግን ከሩቅ የሚመጣ ደካማ ድምፅ ሆኖ ነበር የሚሰማን፡፡ የቤንዚንና የ ቡና በወተቱ* (cafè crème) *ሽታም፣ ተደባልቆ ጎዳናውን አውዶታል፡፡ የመንገዱን ጥግ ተጠምዝዘን መናፈሻወቹን አለፍን፡፡ ልጆች አሁንም ከደማቁ የምሽት ሰማይ ስር ይጫወታሉ፡፡ አዛውንቱ ግን በምሽት ለማንበብ አይናቸው ደካማ ስለሆነ መፅሀፎቻቸውን ከድነዋል፣ ጋዜጦቻቸውንም አጥፈዋል፡፡*

*ኩሩና ቁጡ የነበረው ጥቁር ሀኪም፣ ከሜሪ መኖርያ ቤት ፊት ከመንገዱ ዳር ይንቆራጠጣል፡፡ የመንገዱን ጥግ ይዞ፣ አንዴ ወደላይ ከዚያም ወደታች ይራመዳል፡፡ እኔና ሜሪ ግን ሽማግሌው ጋሪ ነጂ «አሬቴ!»* (Arrêtez) *ብሎ እስኪጮህ ድረስ ከቤትዋ መድረሳችንን አላወቅንም ነበር፡፡ ሀኪሙ አፍጦ በቁጣ እንደሚመለከተን ተገነዘብን፡፡ ከዚያም ሲንደረደር መጥቶ ሜሪን ከጋሪው ላይ ጎትቶ አወረዳት፡፡ ለመሰነባበት እንኩዋን ጊዜ አላገኘንም፡፡ «የባቡር ላይ ቦታዬ እንዳይያዝብኝ እባክሽን ፍጠኝ!» ብሎ ተቆጣ፡፡*

*ወደቤት እንድትገባ ሀኪሙ እያዋከባት ሳለ፣ ሜሪ ዞር ብላ በደከመ ድምፅ፣ «ደህና ሁን! ፍቅሬ! ደህና ሁን! ደህና ሁን!» አለችኝ፡፡*

*«ደህና ሁኝ!» አልኩ እኔም ጋሪው ላይ ቆሜ፡፡ ሽማግሌው ጋሪ ነጂም፣ «አሎን» (Allons) አለው ፈረሱን ጮሆ፡፡ ሜሪም ንዴት ካገነፈለው ሀኪም ጋር በራፉን አልፋ ገባች፣ ካይኔ ጠፋች፣ ተሰወረች፡፡*

*ክሎፕ! ክሎፕ! . . . ክሎፕ! ክሎፕ! . . የፈረሶቹ ኮቴዎች ከመንገዱ ጋር ሲገናኙ . . ክሎፕ! ክሎፕ! . . . . . ክሎፕ! ክሎፕ! . . . . . ጋሪው ይዞኝ ነጎደ፡፡*

*አሁን በቅዱስ ሚካኤል ጎዳና ያሉት መብራቶች ደምቀዋል፡፡ የ ቡና ቤቶቹም በረንዳዎች (cafè terrace) በሰው ተሞልተዋል፡፡ ኖትር ዳም ከደሴቱ ላይ ተጎምልልዋል፡፡ ሴኑን አቋዋርጠን ስንጉዋዝ፣ ሌሊቱ እንደ ሀዘን ጨርቅ ፓሪስን አለበሳት፡፡ ሽማግሌው ጋሪ ነጅም በ ሌ-አል በኩል ወደ ሞማትር አቋዋረጠ፡፡ ክሎፕ! ክሎፕ! . . . . . ክሎፕ! ክሎፕ! . . . .*

የሜሪ ፍቅር እየደበዘዘ፣ ሀዘኑ እየታገሰ፣ ትዝታው እየቀነሰ ሲሄድ፣ «የፅጌረዳ መአዛ» የተሰኘውን ግጥም ፃፈላት፡፡

□□□

ላንግስተን ሂውዝን ከሚከነክኑት ጉዳዮች አንዱ የኢትዮጵያ በጣልያን መወረር ነበር፡፡ «እየተደነቅሁ እንከራተታለሁ» የሚለውን ሁለተኛውን መፅሀፍ ሲደመደም እንዲህ ይላል፡፡ ጊዜው የ 1937-1938 ዘመን መለወጫ ምሽት ነበር፤ እንደ ፈረንጆች አቆጣጠር ማለት፡፡

*ሰው ሁሉ የት ገባ! ምነው ፓሪስን፣ ይህችን አሮጌ ጥንታዊ ከተማ፣ በመጀመሪያዎቹ የአዲስ አመት ሰአቶች ውስጥ ፀጥታ ሰፈነባት! አምና ክሊቭላንድ ነበርኩ፤ ሀቻአምና ሳንፍራንሲስኮ፤ ከዚያ በፊት ሜክሲኮ ከተማ ነበርኩ፣ ከዚያም ቀድሞ ካራሜል፤ ከካራሜል በፊት ደግሞ ታሽኬት ነበር አዲሱን አመት ያሳለፍኩት፡፡ የሚቀጥለውን የት ይሆን የምቀበለው? ጦርነት ይኖር ይሆን-ከፍተኛ ጦርነት? ሙሶሎኒና ሂትለር በኢትዮጵያና በእስፓኛ ላይ የሚያካሂዱትን ግፍ አጠናቀው፣ አይሮፕላናቸውን ወደኛ ይመልሱ ይሆን? ስልጣኔ ይደመሰሳል? አለምስ ታበቃለች?*

*«የለም» አልኩ በልቤ፣ «የኔስ አለም አታበቃም፡፡» ግን አለማት አልፈዋል፤ ብሂሮች ወድመዋል፤ ስልጣኔዎችም ተደምስሰዋል፡፡ በረዶ በተከመረበት ሌሊት፣ የሞማትርን (Montmartre) አሮጌ ቤቶች ጥላ ተገን አድርጌ ራሴን በራሴ አፅናናሁ፣ «የለም» አልኩ እንደገና፣ «የኔስ አለም አታልፍም፡፡» ግን እንዴት እርግጠኛ እሆናለሁ? እንጃ . . ላንድአፍታ መንፈሴ በጭንቀት ተዋጠ፡፡*

እንግዴህ የላንግስተን ሂውዝን የህይወት ታሪክ ለሌሎች ልተወውና ወደግጥሞቹ ላምራ፡፡ ግጥሞቹን እኔ እንደወደድኩዋቸው ሁሉ እናንተም እንድትወድዋቸው፣ ለኔ ልዩ ትርጉም እንደሚሰጡኝ ሁሉ፣ ለናንተም የግላችሁ የሆነ ትርጉም እንድታገኙባቸው እመኛለሁ፡፡

አምሀ አስፋው፡፡
3/20/96 (አ.እ)
ኮሎምቢያ ሚዙሪ፡፡

**ስነ-ፅሁፍ አሳ የሞላበት ሰፊ ባህር ነው።**
**መረቤን ጣልኩ፣ ጎተትኩም፤**
**አሁንም እየሳብኩ ነው።**

*ላንግስተን ሂውዝ*

19

# ኔግሮ ስለወንዞች ይናገራል

አይቻለሁ ወንዞች ብዙ፣
እንደምድር ጥንታዊ የሆኑ፤
አይቻለሁ ወንዞች ብዙ፣
ቀደምትነት ያላቸው፣
        በሰው ዘር ከሚፈሰው ደም ሁሉ፤
መንፈሴም እንደወንዞቹ፣
እጅግ ልቅዋል ጥልቀቱ።

የጊዜ ጎህ ገና ሲቀድ፣ በኤፍራታስ ታጥቢያለሁ፤
በኮንጎ ዳር ጎጆዬን ቀልብሼ፣ በድምፁ አንቀላፍቻለሁ።
አባይን አተኩሬ ተመልክቼ፣ ከበላዩ ፒራሚድን ገንብቻለሁ፤
ኤብ ሊንከን ኑኦርሌንስ የሄደ ዘመን፣ የሚሲሲፒን ዜማ
                        አዳምጫለሁ፤
ጭቃማ ልቡም፣ ፀሀይ ስትጠልቅ ወርቃማ ሲሆን
አይቻለሁ።

አይቻለሁ ብዙ ወንዞች፣
ጥንታዊ፣ ሚስጥራዊ፣ ጅረቶች፤
መንፈሴም እንደወንዞቹ፣
እጅግ ልቅዋል ጥልቀቱ።

# የስርግ ጎዳና ትርምስ

ተደባልቆ፣
ትንፋሽና ሽታ፣
ተጣብቆ፣
ሲተራመስ፣
ጥቁርና ነጭ፣
ሲጋፋ፣
ፍርሀት፣
የለውም ቦታ፡፡

# ድምር

፩ን በ ፩ ላይ ደርቡ፣
እና ተመልከቱ፣
፪ እንደሁ ድምሩ፡፡

ይሆናል እንዲያ ውጤቱ፣
፩፣ ከሆነ ፩ በእርግጡ፡፡

ግን አታስገቡ በመሀሉ፣ ሌላ፣
ሴቶችም ሆኑ ወንዶች ጣልቃ፡፡

# ወንድማማች

እንዛመዳለን አንተና እኔ፣
አንተ ከምእራብ-ኢንዲስ፣
እኔ ደግሞ ከኪንታኬ፤

እንዋገናለን አንተና እኔ፣
አንተ ከአፍሪቃ፣
እኔ ደግሞ ከዩ-ኤስ-ኤ፣

ወንድማማች አንተና እኔ፡፡

# ሀርለም

ምን ይሆናል ተስፋ፣
የታለፈ በይደር?

ይደርቃል
እንደተሰጣ ዘቢብ?
ወይ ይመረቅዛል እንደ ቁስል-
ከዚያም አልፎ እንደሚመግል?
ይጠነባል እንደከረመ ስጋ?
ወይ ይፈሳል ገንፍሎ-
እንደስኳር ድፍድፍ ከፍፎ?

ይጠረመስ ይሆናል ምናልባት፣
እንደከባድ ጭነት፡፡

ወይስ ይፈነዳል?

# ጉራማይሌ ዘፈን

ቢኖረኝ ኖሮ ልብ፣ የወርቅ፣
አንዳንድ ሰዎች፣ የማውቃቸው፣ እንዳላቸው፣
ተነስቼ፣ የወርቅ ልቤን ሽጬ፣
እጉዋዝ ነበር፣ ወደሰሜን፣
ብሬን በጄ ጨብጬ፡፡

የወርቅ ልብ፣ የለኝም ግን፣
አይደለምና የኔ፣ እርሳስም፣
የተሰራ ነው ከጆርጅያ አፈር፣ ከጥንቱ፣
ይሄ ነው እንግዴህ ምክንያቱ፣
የልቤ ቀይነቱ፡፡

ይገርመኛል፣ ቀይ አፈር ቀይነቱ፣
የጆርጅያ ጠፈር ሰማያዊ መሆኑ፡፡
የእኔ እሽታ በቁሙ፣
ይገርመኛል፣ ላንተ ሲሆን
ወደ እሽ ጌታዬነት መቀየሩ፡፡

ይገርመኛል ሰማዩ ሰማያዊነቱ፣
አፈሩም ቀይነቱ፣
ለምን ይሆን ታች አገር፣ ደቡብ፣
ሁሌ ከታች መሆኑ፣
አለመውጣቱ ወደላይ፣
ከስር ሆኖ መቅረቱ፡፡

# ጦር ሳይከተት

ስማኝ ጆ!

አታውቅም እንዴ፣
ነገ፣
እንዳለብህ መሄድ፣
አረሩ ከሚነፍስበት፣

ባህር ማዶ፡፡

ስማኝ ጉብል፣
የነገው እጣህ ተፅፍዋል፣
ከሩቅ አገር እንደምትሞት፣
ዝናቡ ከሆነበት ጥይት፡፡

አትጠይቀኝ፣ ብለህ ለምን፣
ብቻ ሂድና ሙት፣ ከዚያ ምድር፣
ትወድቃለህ ከሜዳ፣ ከመቃብር፣
ባንተ ምትክ፣ በሰው ፈንታ፣
ይሰጣል ለዘመዶችህ ሜዳልያ፣

አያልቅሱ እባክዎ፣ እማማ፡፡

## የጃጀ የከፋ ትናንት

ያ ክፉ ትናንት፣ አሮጌ፣
ይከተለኛል ከሁዋላዬ።
ድርጊቴ፣ ወሬዬ፣
ሆኖብኛል ፍዳዬ።

አምና የሰራሁት፣
ምን አገናኘው ከዛሬ?
ያለፈው ክረምት በረዶ እንኩዋን፣
ቀልጦ ጠፍቶ የለም እንዴ።

ባለፈው ሳምንት የሆነውን፣
መስሎኝ ነበር የረሳሽው፣
ግን ዛሬ ጥዋት ስንገናኝ፣
ምነው ንግግር ነፈግሽኝ፣
ምነው ፊትሽን አዞርሽው።

ትውስታሽ እንደዝሆን፣
መርሳትን የማታውቂ!
እንዲያ ከሆነ ስሜትሽ፣ ሆዴ፣
ያልማገዝ ቀለበቴን መልሺ።

## ክትመት

እያከተመ ይመስለኛል ህይወቴ፣
ቀሪው ጊዜዬ፣ እድሜዬ፣
ይመስለኛል እያለቁ ቀኖቼ፣
የምሬን ነው፤ ሽንኮሬ!

ይሄው ነው እንግዴህ ምክንያቴ፣
ሌሊቱን ካንች የማጥፋቴ።

# ወገኖቼ

ሌሊቱ እጅግ ውብ ነው፣
የወገኖቼም መልክ እንዲሁ፣
ከዋክብቱ ውብ ናቸው፣
የወገኖቼም አይኖች እንዲሁ፣
ውብ ናት ፀሀይትዋም፣
ውብ ነው መንፈሳቸው፣ የወገኖቼም እንዲሁ፡፡

# ደንቃራ

እችላለሁ ልነግራችሁ፣
ብፈልግ፣
እኔን፣
እኔ እንዳደረገኝ ምን፣
ግን፣ ልነግራችሁ፣
እኔም አልወድ፣
እናንተም፣
የላችሁ ግድ፡፡

# ስሞታ

ገንዘብና ኪነት፣
ልይታቸው፣ አቤት!

# አንጎላ የጥያቄ ምልክት

አይገባኝም ሚስጥሩ፣
እኔ ጥቁሩ፣
መቆሚ ጀርባዬን ሰጥቼ፣
ለመጨረሻው የፍርሀት ድንበር ተጋልጬ፣
በኔው ምድር፣ በሀገሬ፡፡

አይገባኝም እኔ፣ ለምን እንደምሸፍት፣
ለምን እንደሚነሳ እጄ፣
በሰው ልጅ ላይ፣ በወገኔ፣
ለመኖር ስል በወንዜ፣ በሀገሬ፡፡

ግን ይኸው ነው፣ እንዲያም ሆኖ፣
ይታወቀኛል፣ ያንተና የእኔ እጣችን፣
እንደሆነ እሮሮ፡፡

27

# ስለመኖሪያ ቤት ትንሽ እንጉርጉሮ

ይሄው እንግዴህ፡
እድሜዬን ሙሉ ሳጠራቅም ኖሬ፣
ማለፊያ ቤት ልገዛ መጣሁ፣
ለኔና ለሚስቴ።

*ነፎች ግን ትፈረጥጣላችሁ --*
*እንዳያችሁ፣*
*ችግሬንም፣*
*እኔንም!*

ሰፈሩ ንፁህ ነው፣
ቤቱ ግን አሮጌ፣
ዋጋው እጥፍ ይሆናል፣
ሲሸጥልኝ ለኔ፤
ምን አረጋለሁ፣ እገዛለሁ።

*ነፎች ግን ትፈረጥጣላችሁ --*
*እንዳያችሁ፣*
*ሚስቴን፣*
*እና እኔን!*

የሚከተለው እንግዴህ፣
የጎረቤቶቻችን መልክ ይጠቁራል፣
የከረሜላው ሱቅ፣
የመሸታ ቤት ይሆናል፣
ነፎች እንደሁ ለቀቁ፣
ሰፈሩን እንዳለ ጥለው፣
ለኔ፣ ለጥቁሩ።

*ነፎች ጥለው ሸሹ፤*
*አለሁ እኔ ከዚሁ፣*
*ፈረጠጡ ነፎች፣*
*እኔ ፍንክች!!*

# የሉሙምባ መቃብር

ሉሙምባ ጥቁር ነበር፣
        ያላደረበት እምነት፣
በነዚያ የተኩዋኩዋሉ ሽርሙጦች፣
        በዩራኒዩም ዱቄት፡፡

ሉሙምባ ሆኖ ጥቁር፣
አላመነም ነበር፣
ዘራፊዎች የሚነፉትን ውሸት፣
በ «ነፃነታቸው» ወንፊት፡፡

ሉሙምባ ጥቁር ነበር፣
        ቀይ የሆነ ደሙ፣
ገደሉት፣
        ወንድ በመሆኑ፡፡

ወረወሩት ሉሙምባን፣
        ህውልት ከሌለው መቃብር፣
ግን አያስፈልገውም ምልክት፣
        መቃብሩ ነውና አየር፡፡

ፀሀይ ናትና መቃብሩ፣
ህዋ ነውና መቃብሩ፣
ጨረቃና ከዋክብት ሁሉ፡፡
ልቤ ነውና መቃብሩ፣
ተከትብዋል ከዚያ ስሙ፣
ነገ ደግሞ፣
        ይፅፈዋል ባለም ሁሉ፡፡

# ጃይሚ

ይጎስማል ከበሮውን፣
        ከኮረብታ ተቀምጦ፣
ለሀያል የምድር አማልክት
        ለማይታዩ ጨርሶ፡፡

ይቀመጥና ከኮረብታ፣
        ባህር ባህሩን ያያል ፈዞ፣
ወደዚያ የህልም አገር
        ወደ'ማይሆን እውን ከቶ፡፡

# ጭቆና

አሁን፣
ህልም አልሆነም፣
        ላላሚዎች፣
መዝሙርም ለዘማሪዎች፡፡

አንዳንድ ምድር፣
ጨለማ ሌሊት፣
ክፉ አረር፣ ጨካኝ ብረት፣
ነግሰዋል በእርግጥ --
ግን ይመለሳል ተስፋ፣
ያስተጋባል መዝሙርም እንደገና፣
ሰብሮ፣
  የታሰረበትን ካቴና፡፡

# አፄ ሀይለስላሴ

(የነፃነት ቀን፡፡ መጋቢት 5/1966 አ.እ)

ሰውነቱ፡ … ህያውነቱ …
የጊዜያችን መሆኑ፣
ተአምር ይመስላል ታላቅነቱ፣
ግርማውና ሞገሱ፡፡
ሆንዋልና አርማችን፣
የጥቁርነታችን፣
ክብራችን፣ … መናችን፣
ንጉሰ ነገስት ወይም የይሁዳ አንበሳ ላልሆኑ፣
የኩራታቸው ምንጭ ነው፣
ያን ታላቅ ቀን በተስፋ ለሚጠብቁ፤
የሚቀዳጅበትን ጊዜ ማህበራዊ ንጉስነት፣
በሚያየው ፍጥረት ላይ ሁሉ፣
የሰው ልጅ አብሮ በአንድነት፤
እያንዳንዱ ሰው ይካፈል ዘንድ ከብርታቱ፣
የገነባውን በግርማው፣
የገነባውን በሞገሱ፤

ኩሩው አፄ፣
የተስፋችን ምልክት፣
የሚኖር ለዘለአለም፣
የማይዳፈን የማይሞት፡፡

# አቃቤ ተስፋ

አምጡልኝ ምኞታችሁን ሁሉ፣
እናንት አላሚዎች ለኔ፣
አምጡልኝ የልባችሁን ዝማሬ፣
እንዳስቀምጠው በወላንሳ ጠቅልዬ፣
ከአለም የፍዳ ጣቶች ሁሉ አርቄ፡፡

# እባክዎ ይግለፁልኝ

አያለሁ ጋዜጦች ሲታተሙ፤
የሚገርም የሚያስቅ ነገር ያዘሉ፡፡
ትዋጋለች ለነፃነት እንግሊዝ፣
ግን አይደለችም ነፃ ህንድ፡፡
ይነግሩኛል ሳምንታዊ ጋዜጦች፣ የጥቁሮች፤
ከእንግሊዝ ቅኝ ግዛቶች፣
ነጩ አሁንም እንዳለ በእግሩ ቆሞ፣
ጥቁር ሰው ግን ከበታቹ ተንበርክኮ፡፡
ጋዜጦቹ፣ የጥቁሮቹ፣ ይነግሩኛል፤
የዘር አጥር ከአፍሪቃ፣ ጥብቅ ነው ይሉኛል፡፡
ታዲያ እንግሊዞች ነፃነት ብለው ሲጮሁ፣
እውነት ትክክል ይሆኑ?
በጭስና በጭጋግ ቢሆንም ያለሁት ታፍኜ፣
እየጣርኩ ነው ለመረዳት አጥብቄ፣
ሰዎች መስጠት እንዴት እንደሚችሉ ለኔ፣
ነፃነት ባፋቸው፣
ፋንድያ ግን በእጃቸው፡፡

# ወደባህር መልስ

መመለሴ ነው ወደ ባህር፣ ዛሬ፣
ንፋስ ሰብቆት አረፋ ወደ ሚቀዝፈው መሄዴ፡፡
መመለሴ ነውና ወደ ባህር ዛሬ፣
ይሰማዋል ሰውነቴ፣ ካገር ከወንዜ መድረሴ፡፡

የገባሁ ያህል ነው፣ ተመልሼ ከቤት፣
ከዚህ መርከብ፣ የብረትና የእንፋሎት፣
ያገኘሁ ነው የመሰለኝ፣ እንደገና፣
የምኞቴን ስባሪ ዳርቻ፡፡

# ጉልላት

ነፃነት፣ ጣፋጭ ዱቄት ነው የተነፋ፤
ጉልላት፣ በሰው ባቡቴ ላይ የተደፋ፤
እንዲያ መሆንም አለበት፣
መጋገር እስከለመድን 'ለት፡፡

# የመንግስት ማስታወቂያ

ክቡር ሞት፡
ደረሰኝ መልእክቱ፣
ልጄ ማረፉ መሞቱ፤
ቀለሙ የተጠቀምህበት፣
ልጄ የፈሰሰው ደም ነው፣
ደብዳቤውን የፃፍክበት፡፡
ክቡር ነው አልከኝ ሞቱ፣
በጦር ሜዳ መሰዋቱ፣
እኔንም ሆነኻል አልከኝ ክቡር፣
በዚህ በደም መኽር፡፡
ደብዳቤህ፣
ተፈርምዋል በደም፣
በልጄ ደም፣
ታትምዋል፡፡

# አዲስ ልብስ

አለችኝ እናቴ፣
አትንበርከክ ልጄ፣
አዲሱን ልብስ ለብሰህ፣
እባክህ፤

እሺም አልኩ፣ እማምዬ፣
እታች ነው ያለሁት፣ አንድዬ፣
መቆየት አልችልም እንዴ፣
ከመሬት፣ አዲሱን ልብስ ለብሼ?

እናቴም፣
እንግዴህ ብያለሁ፣ አለች አይሆንም!
ይፈፀም ነበርና ያለችው እናቴ፣
ይሄው ነው ምክንያቱ፣
ዛሬ ንፁህ የመሆኔ፣
አዲሱን ልብሴን ለብሼ፡፡

# ጆል እንሰሶች

ውሻው መንገዱን ተከትሎ ሮጠ፣ ወደታች፣
አሸንዳውን ይዛ ወደላይ፣ ድመትዋ፤
እነዚህ ደሞ ጀመሩ! አለች፣
እየቻቸውና አይጥዋ፡፡

## እንቆቅልሽ

፩ እና ፩፣ ፪፤
፪ እና ፪፣ ፬፤

ግን ምን ይባላል፣
ዘግይቶ ቢደርስ ሁለተኛው ፪?

ምን ይፈጠራል፣
እኔ ብሆን አንዱ ፩?

ወይም አንተ ብትሆን፣ የመጀመሪያው ፪ -
ሲካፈል ለሁለት?

## ተስፋ

የሙጥኝ በሉ ተስፋችሁን፣
የሞተ እንደሁ ተስፋ፣
 ህይወት ወፍ ነውና፣ የተሰበረ ክንፉ፣
 ያቃተው የተሳነው መብረሩ።

የሙጥኝ በሉት ህልማችሁን፣
የጠፋ እንደሁ ተስፋ፣
 ህይወት ማሳ ነውና ባዶ፣
 ያቀረፈደው በረዶ።

# ፀሎት፣ ለክረምት ሌሊት

ኦ! ታላቁ የክረምትና የብርድ አምላክ፣
መሬትን በበረዶ ጋቢ ጠቅልላት፣
እና፣ አቆራምዳቸው በብርዱ፣ ደሆችን ካሏቸው፤
የሚደርቡት ልብስ የሌላቸውን፣ 'ሚያሞቃቸው፣
ወይም በቂ ምግብ፣ ጥንካሬ 'ሚሰጣቸው፣
እባክህ አንተ አምላክ፣ አቆራምዳቸው እንጅ በብርድ፣
                    አቆርፍዳቸው፣
ይደንዝዝ እጅ እግራቸው፣
መምታት ያቁም ልባቸው፣
እንዲነቁ ማልደው፣
        ከበለፀገ ምድር ከተዋበ፣
የት እንዳለ ካልታወቀ፡፡
ሁለንተናው ምንምነት፣
ምንምነቱ ደግሞ፣ ሁለንተናው ከሆነበት፡፡

# የሰፈር ስብሰባ

መሰላል በንዲራና የድምፅ ማጉያ ነው፣
        መለፈፊያቸው አሁን፤
ድሮ፣ የሳሙና ሳጥን እንዳልነበር፡፡
ተናጋሪው ይንቦገቦጋል እንደ እሳት፣
ቁልቁል እያዩ ያዳማጪን ሁሉ ፊት፣
ቃሎቹ ካፉ ይወድቃሉ ወደመሬት ወደታች፣
ቦታቸውን ለመያዝ፣
        ለመሆን አዳማጭ ተመልካች፡፡

# ይዘት

ጎረምሳ ልጅ መጣ፣
 የሰው አሳ ተሸክሞ፣
ከትከሻው አንግቦ፣
ግማሽ ሰው ግማሽ አሲትዋ፣
ጭራዋን ቆልምማ፣ ከብብቱ ከታ፡፡

አጥማጅ ስለሆነ ልጁ፣
 አሳ አገኘ 'ሚሸከመው፣
ግማሽ አሳ፣
 ግማሽ ኮረዳ የሚያገባው፡፡

# የአሜሪካ ሰቀቀን

ያሜሪካ ሰቀቀን ነኝ፣
ድንጋይ፣
 ነፃነት የተደናቀፈበኝ፣
አውራ ጣቱን ያጎነበኝ -
ከባድ ስህተት ነኝ፣
ጀምስ ታውን የሰራኝ፤
ድሮ፡፡

# የፅጌረዳ መአዛ

ፍቅር እንደጤዛ ነው፣
በንጋት አበባ ላይ እንደተኮለለ፣
አጅሬ ፀሀይ ሲወጣ፣
ይሆናል እንዳልነበረ።

ፍቅር እንደኮከብ ብርሀን ነው፣
በጥዋት ሰማይ 'ሚያንፀባርቅ፣
ብርሀነ ኮከቡ ያልፋል፣
ይጠፋል፣ ቀን ሲወለድ።

ፍቅር እንደሽቱ ነው፣
የሚኖር በፅጌረዳ ልብ ተቀብሮ፣
አበባው ይጠወልጋል፣
ሽቱም ይተናል አብሮ።

የተሻለ አይደለም ፍቅር፣
ከፅጌረዳ ሽታ፣
አይሻልም ከቶ፣
ከፅጌረዳ መአዛ።

# የራስን ህይወት ለማጥፋት ኑዛዜ

ፀጥታ የሰፈነበት፣
የወንዙ ፊት፣
ቀዝቃዛው፣
ጠየቀኝ እንድስመው።

# የሁለት ሌቦች ቅንቅን*

ክርስቶስ ሲሞት በጎልጎታ፣
አሁን እንደምናምነው፣
በግራ በቀኙ፣
ሌቦች ተሰቅለው ነበር፣ አብረው።
ሁለት ወራዳ ወሮበሎች፣
የ'ለት ምግባቸውን የሚሰርቁ፣
ታስረው ነበር ከመስቀል፣
በፋንታው ሞትን እንዲቀምሱ።

አንዱ ሌባ፣ እንዲህ አለ፤ ክርስቶስን አየና፡

ታላቅ ከሆንክ እውነት፣
ተከታዮችህ እንደሚሉት፣
እስቲ ራስክን አድን! እኔንም፣
አጠገብህ ያለውን፣ ሌባው ጉዋደኛዬንም።
ታላቅ ከሆንክ እውነት፣
ተከታዮችህ እንደሚሉት።

ግን ቀላጤ አልነበረም ለሌባው ወንድሙ፤
ለተንጠለጠለው ከመስቀሉ።
ሌላው ሌባ ጮሆ፣
አምላኬ አትርሳኝ በማለቱ።

ክርስቶስ አጥልቆ ነበር፣
የሾህ አክሊል ከራሱ፤
መራራ ሀሞት ሞልቶ ባፉ፣
ይፈስ ነበር ከመዳፉ፣
ይፈስ ነበር ከመሬት፣ ደሙ።

** ቅንቅን = Ballad (ዶክተር ጌታቸው ሀይሌ)*

ለሰው ሀጢአት ነውና ስቃዬ፣
ለሰው ሀጢአት ነውና ሞቴ፣
ለጩኸትህ መልስ ይሁኑ፣
ስጋዬና ደሜ፡፡

በመናፈሻ ውስጥ አንዱ ከዳኝ፣
ጴጥሮጥም ካደኝ ሶስቴ፣
ግን አንተ እንዳትረሳኝ ብለህ የምትጮህ፣
ትሄዳለህ ወደገነት፣ አብረህ ከኔ፡፡

# ነፃነት - ፩

አንዳንዶች፣
መፅሀፍ በማቀጠል፣
ይመስላቸዋል ያቃጠሉ፣
ነፃነትን፣

አንዳንዶች፣
ኔህሩን በማሰር፣
ይመስላቸዋል ያሰሩ፣
ነፃነትን፣

አንዳንዶች፣
ጥቁር ሰው አሳዶ በመግደል፣
ይመስላቸዋል የገደሉ፣
ነፃነትን፡፡

ነፃነት ግን ስቆ፣
ከፊታቸው ቆሞ ተንከትክቶ፣
ይላቸዋል፣

እኔ እንደሁ አልሞት፣ አልገደል!

# የምኞት አይነት

እጆቼን በሰፊው ዘርግቼ፣
ተሽከርክሬ ዳንኪራዬን መትቼ፣
ከሚሞቅበት ቦታ ፀሀዩ፣
እስኪያከትም ይህ ቀን፣ ነጩ።።
አርፋለሁ ከዚያ በቀዝቃዛው ምሽት፣
ከረጅም ዛፍ ተጠግቼ፣
ሌሊቱ ሲመጣ ረጋ ብሎ፣
እንደኔው ጠቁሮ ጨልሞ፣
ይሄው ነውና ምኞቴ!

እጆቼን በሰፊው ዘርግቼ፣
በፀሀይ ፊት ቆሜ፣
ጨፍሬ፣ ሾሬ፣ ተሽከርክሬ፣
አጭሩ ቀን ሲያበስር፣
አርፋለሁ በደብዛዛው ምሽት…
ከመለሎ ዛፍ ስር….
ሌሊቱ ሲመጣ፣ ደጉ እምዬ፣
የጠቆረው እንደኔ።።

# የባህር ፀጥታ

ይገርማል ዛሬ ባህሩ፣
መከበዱ፣ መርጋቱ።።
አለመነሳቱ ማእበል፣ መዋጡ በፀጥታ፣
ጥሩም አይደል ለባህር፣ ደግም አይደል ለውሀ።።

# ፍርሀት

ከሰማይ ጠቀስ ህንፃዎች ስር፣እንጮሀለን፣
የአፍሪቃን ዘንባባዎች ተጠግተው፣
          እንዳለቀሱ ሁሉ አባቶቻችን፡፡
ብቻችንን ስለሆንን፣
ስለጨለመ፣
          ስለፈራን፡፡

# የቸገራት ሴትዮ

ቆማለች፤
እርጭ ባለ ጨለማ ውስጥ፣
አንድ ሴት የቸገራት፣
ተደፍትዋል አንገትዋ፣
ተጭንዋት ህመምዋና ድካምዋ፤
እንደመፀው አበባ፣
          በረዶ እንደመታው፣
እንደመፀው አበባ፣
          ነፋስ እንደገረሰሰው፣
ራሱን እንደማያቀና፣
እንደገና፡፡

# ልጅነት

ነገ ይታያል፣
  ከፊታችን ቆሞ፣
እንደ ነበልበባል ብሩህ ሆኖ፡፡

ሌሊት ነው ትናንት፣
               ያለፈ፣
ፅሀይም የጠለቀ፡፡

እና ዛሬ የማለዳ ጮራ፣
ቅስት ነው፣
  ላለፍንበት መንገድ የተሰራ፡፡

ወደፊት!

# የሜዳ አበባ

የሜዳ ውብ አበባ፣
ሞተች ጠወለገችና፡፡

የቀን ሰዎች ሳቁ፣
የሌሊቶቹ ደግሞ አለቀሱ፡፡

የሜዳ ውብ አበባ፣
ሞተች ጠወለገችና፡፡

# የምድር ዜማ

ዝማሬ ነው የምድር፣
        የጠበቅኩት ብዙ፣ ልሰማ፣
የአለም ድምፅ፣
        የአለም ዜማ፡፡

መዝሙር ነው የፀደይ፣
የጠበቅኩት ብዙ ልሰማ፤
        ሀይለኛ እንደ እንቡጥ፣
        ሀይለኛ እንደ ቡቃያ፣
        ሀይለኛ እንደሆነ የበኩር ልጅ፣
                ከናቱ ማህፀን ሲወጣ፡፡

የአለም ዜማ፣
የአካል ዜማ፤
የፀደይ ዜማ፣
ጠብቂያለሁ ለዘመናት፣
        ይህንን የምድር መዝሙር ልሰማ፡፡

# ፀሎት

ልጠይቅህ፣
 ወዴት ልጉዋዝ?
ልጠይቅህ፣
 የቱን ሀጢአት ልሸከም?
 የቱን ዘውድ ልድፋ?
ጨነቀኝ፣
 አምላኬ ሆይ፣
ጨነቀኝ፡፡

# የተስፋ ቡጊ

እንደምን አደርክ አብዬ!
አልሰማህም እንዴ፣
የቡጊ ውጊውን አታሞ፣
በይደር የተያዘውን ተስፋ ርምራሞ፡፡

አዳምጥ ጠጋ ብለህ፣
ይሰማሀል እግራቸው፣
ሲል ሲመታ፣

ይመስልሀል ልበል፣
ምቱ የደስታ?

አዳምጥ ጠጋ ብለህ፣
እና አይሰማህም ከጀርባው፣
የሚል እንዲህ፣

ምን ነበር እኮ ያልኩህ?

ድንቄም!
ተደሳች ነኝ፣
ይልቅስ ተቀበለኝ፣

ሄ-ፖፕ፣
ራ-ቦፕ፣
ሞፕ፣
ዬ!!

# ለማኝ ልጅ

ይህ ለማኝ ልጅ፣
ምን አዝሎ ይሆን በውስጡ፣ ተሸክሞ፣
የማልሰማው የማይሰማኝ፣
የማላዬው፣ ወይም ደግሞ፣
የማላውቀው የማይገባኝ፣
ሆኖም ግን የሚጠራኝ።

አይደለምን የፀሀይ ጥላ፣
ነፍስ የዘራበት መልከ ጥፉ፣ ያፈር ሸክላ፣
እንዲያም ሆኖ ይንቀረቀራል ከዋሸንቱ፣ ነፃ ቃና፣
እድል በካራ እንዳልወጋችው፣ እንዳልደማ።

# ግድግዳዎች

አራቱ ግድግዳዎች፣
ችለዋል ስቃይ ብዙ፣
አራቱ ግድግዳዎች፣
ከንፋስ የሚከልሉ፣
ከዝናብ የሚጠልሉ።

አራቱ ግድግዳዎች፣
ችለዋል ብዙ ሀዘን፣
ከትናንት ያዳኑት፣
ለነገ ግን የሚሆን።

# ለአንዳንድ ምሁራን

አይደላችሁም ወዳጆቼ፣
ደሀ በመሆኔ፣
ጥቁር በመሆኔ፣
ደንቆሮ ፈዛዛ አይደለሁ፣
ከናንተ የተለዬሁ።
እናንተው ናችሁ፣
የነገራችሁኝ እንዲያ ብላችሁ፣
የለም፤ ወደጆቼም አይደላችሁ።

# ጥያቄ

ቁሻሻ ጠራጊው አዛውንት፣
ሲመጣ አጅሬ ሞት፣
ሲሰበስብ አፅማችንን፣
        ሊወረውር ከምንምነት ከረጢት፣
ያገኘው ይሆን የነጬን ሬሳ፣
የባለብዙ ሚሊዮኑን ጌታ፣
ሆኖ የሚያተርፍ፣
        ዘለአለማዊ ቤሳ፣
ከጥቁር ሰው አስከሬን ይልቅ፣
        ከጥጥ ለቃሚ ባርያ።

# የመፀው ግጥም

በቀለም የደመቁ፣
የመፀው ቅጠሎች፣
የቮልካንን ጎዳና ያካልላሉ፣
መለሎ፣ የሚያማምሩ ዛፎች፣
ቀይ የለበሱ፣
በወርቅ ያጌጡ፣
ይመስላሉ ወጣት ሴቶች፣
አፍቃሪዎቻቸውን 'ሚጠብቁ፡፡
ግን ሳይቆይ፣ የክረምቱ፣
ያስቀራቸውዋል እርቃናቸውን፣ ነፋሱ፣
ከዚያም፣ ቁሩ በረዶው፣
ሆኖ ይቀራል፣ የሚያብስ፣ የሚዳስስ፣
የብቸኛ ፍቅራቸው፡፡

# የመጋቢት ጨረቃ

እርቃንዋን ናት ጨረቃዋ፣
ንፋስ ልብስዋን ገፍዋት ከላይዋ፣
ንፋስ ወስዶባታል፣ ደመና ካባዋን ጠራርጎ፣
የጨረቃን አካል ገልቦ፣
እና አሁን ነች ራቁትዋን፣
ጨርሶ ባዶዋን፡፡

ለምንድነው የማትሸኮረመሚ፣
አንች ጨረቃ የማታፍሪ?
አታውቂም እንዴ መሆኑን ነውር፣
መራቆት መገለብ?

# አርዴላ

ባያበሩ ኖሮ አይኖችሽ፣
ቦግ ባይሉ እንደፀሀይ፣
እመስልሽ ነበር፣
ከዋክብት ባልፈነጠቁበት፣
ጨለማ በዋጠው ሰማይ፣
ዘፈኖችሽ ባይኖሩ፣ ውብ ድምፅሽ ባይሰማ፣
እመስልሽ ነበር በ'ንቅልፍ፣
በህልም አልባ መኝታ።

# የበሽተኛ ክፍል

ፀጥታ ውጦታል፣ ምንኛ፣
ይህን ክፍል፣ የበሽተኛ፣
ካልጋው ላይ፣
ተኝታለች፣ አንድ ሴት፣ 'ማትናገር፣
በሁለት አፍቃሪዎችዋ ፣
በህይወትና በሞት መሀከል፣
ሸፍኖአቸዋል ሶስቱንም፣
የህመም ጋቢ፣ የጣር።

# የማለዳ መንገደኞች

መንገደኞች ነንና፣ ከጎህ ጋር ከማለዳ፣
መንገደኞች ነንና፣ ከፀሀይ ጋር ከማለዳ፣
አያስፈሩንም ቀናት፣ የመከራ፣
ወይም ሌሊት ጨለማ፤
ከፀሀይና ከማለዳ ጋር መንገደኞች ነንና።

# ዘዴዎች

የእጅን የደም ስር መቁረጥ፣
የሚያቃጥል አሲድ መጠጣት፣
አንጎልን መበርቀስ በጥይት፣
ከዚያም፣ ይመጣል ሊታቀፍህ ሞት፣
እንደወላድ ሁሉ፣ እንደ'ናት።

# ሶስና ቀይ ስትለብስ

ሶስና ዮሀንስ ቀይ ስትለብስ፣
        እንደጥንታዊ እንቁ ነው ፊትዋ፣
ጊዜ እንዳረገው ሽክላማ፡፡

ታጅበህ ና በመለከት፣
እግዚአ መሀረነ ክርስቶስ!

ሶስና ዮሀንስ ቀይ ስትለብስ፣
ትሆናለች ንግስት የምትራመድ ተነስታ፣
ከምስራዊ ሌሊት፣ ከሞተ ከተረሳ፡፡

ይነፋ መለከት፣
እግዚአ መሀረነ ክርስቶስ!

ሶስና ዮሀንስ ቀይ ስትለብስ፣ ውበትዋ፤
ይነዳል እሳት ከልቤ ውስጥ፣
  የሚቀስፍ ህመሙ የሚወጋ፡፡

ጣፋጭ የብር መለከት፣
እግዚአ መሀረነ ክርስቶስ!

# የክርስቲያን አገር

እግዜር ያንቀላፋል፣ ከጠባብ የጉዋሮ መንገድ ተኝቶ፣
የጅን ጠርሙስ ጨብጦ፣
ና እንጅ ምነው እግዜር፣ ተነሳ፤
እንደወንድ ልጅ ሁን፣ ተዋጋ፡፡

# እንጉርጉሮ

ደንታዬም አይደል አላባማ፣
ጉዳዬ፣
አገሬ ቢሆንም፣ ወንዝዬ።

# ምክር

እውነቱን ነው የምላችሁ፣ ሰዎች፣
መወለድ እጅግ ከባድ ነው፤
መሞትም አስከፊ ነገር፤
በሁለቱ መሀል ግን፣
አይከፉም ትንሽ መፋቀር።

# ጊዜያዊ ፍቅር

ዜማ ነሽና ለኔ
ልዘፍንሽ አይገባኝም ሁሌ፡፡

አልደግምሽም በያለበት፣ እኔ፣
ስለሆንሽ ፀሎቴ፣ ሱባኤዬ፡፡

ፅጌረዳዬ ነሽና
አትቆይም ካለሽበት፣ በጋው ሲያከትም ሲወጣ፡፡

# ድካም

አልሰለቻችሁም እንደኔ፣
        መጠበቁ፣
እስክታምር እስክትጠራ፣
        አለም እኪጠናወታት ደግነቱ?
ኧረ እንግመሳትና በሴንጢ፣
የሚቦጠቡጥዋትን ትሎች እንይ እስቲ፡፡

# ይሻላል

ጭር ባለ ሌሊት ለብቻዬ፣
ማልቀስ ይሻለኛል ተቀምጬ፣
አቅፌ ከማነባ፣
አንች ሄደሽ፣ ካንች ሌላ።

ባማረ ቀን ባሸበረቀ
በፀሀይ እና በዜማ፣
ይሻለኛል ባላዳምጥ ሙዚቃ፣
ያንች-ያልሆነ ድምፅ ከምሰማ።

# አዲስ ጨረቃ

ተወልዳለች፣ አዲስ ጨረቃ፣
የምትጋልብ በኮረብታ፣

ፍንዱቅ አዲስ ጨረቃ፣
ደመናውን 'ምታጠና፣

አይን አፋር ወጣት ሆና፣
ፊትዋን ሸፍና ጋርዳ፣
ፍቅርዋን እንደምትጠብቅ ኮረዳ።

# ታሪክ

ያለፈው ነገር ተፅፍዋል፣
በደምና በዋይታ፣
መሆን ግን አይገባውም፣
የወደፊቱ እውነታ።።

# የኢትዮጵያ ጥሪ

ኢትዮጵያ፣
አቅኝ ፊትሽን፣ ጥቁሩን ጨለማ፤
አበሻ፣
የሳባ ልጅ ዝርያ!

ዘንባቦችሽ ረጃጅም፣
ተራሮችሽ የመጠቁ፣
መጠለያ ናቸው ጋሻ፣
ለነፃነት ሲሉ ለሚወድቁ፤
በመስዋእትነትሽ ፈለግ፣
መላው አፍሪቃ ይነሳ፣
አይኑ እሳት ጎርሶ፣
ፊቱ ድቅድቅ ጨለማን ለብሶ፣
የሳባን ዘር ጥሪ ሰምቶ፤

ነፃ ናት ኢትዮጵያ፣
እናንተም ሁኑ እንዲያ፣
መላው አፍሪቃ፣
ተነሱና ሁኑ ነፃ!
የጥቁር ህዝቦች ሁሉ፣
ሁኑ ነፃ! ሁኑ ነፃ!

# ፍትህ

የምትለውን ፈሊጥ፣ ፍትህ እውር ጣኦት ናት፣
ውለን አድረናል ጥቁሮች፣ ካወቅን ከነቃንባት፣
ሻሸዋ የሸፈናቸው፣ ሁለት የመረቀዙ ቁስሎች፣
ምናልባት አንዴ ነበሩ፣ የሚያዩ ትላልቅ አይኖች፡፡

# መንግስተ ሰማያት

መንግስተ ሰማያት፣
ነው የተሞላ ቦታ፤
ዳር እስከዳር፣
በደስታ፡፡

እንሰሳት ይዘምራሉ፣
ወፎችም እንዲሁ፤
ሌላው ፍጡር፣
እንደሚያደርገው ሁሉ፡፡

እያንዳንዱን ድንጋይ ስታልፉ፣
ትላላችሁ፣ «አቶ ድንጋይ እንደምን አሉ?»
«ደህና! የእርሶስ ጤና ጌታዬ?»
ይላል ሲመልስ፣ ድንጋይም በበኩሉ፡፡

# ሀምራዊ ምኞት

ይመታ ነጋሪት ለኔ፣
ይመታ ነጋሪት፣ የመከራና የሞቴ፣
መዘምራኑ ያሰሙ ድብልቅልቅ ያለ ዜማ፣
የሞቴ ጣር እንዲሸፈን፣ ተውጦ እንዳይሰማ፤

ምቱልኝ የመከራን ነጋሪት፣
ነጩ መሰንቆ፣ ይስለል፣
        ድምፁም ይቀዝቅዝ ይሙት፤
ግን ይነፋልኝ መለከት፣
        እንደፀሀይ የሚያበራ ቃና፣
ተከትሎኝ የሚሄድ፣
        ወደምግዋዝበት ጨለማ፡፡

# መሹለኪያዎች

ጥልቅ ነው ባህር፣
ጨቤም ስል፣
መርዝም ቅጥል፤

ግና፣ ሁሉም ያስገኛሉ እረፍትን፣
ሁሉም ይሰጣሉ ሰላምን፣
የደከመች ነፍስ የምትመኘውን፤
ሁሉም ያስገኛሉ እፎይታ፣
በዘለአለማዊ ምንምነት፣
የገባች ነፍስ ከማትወጣበት ተመልሳ፡፡

# የግል

በፖስጣ፣
  ተብሎ፣ ነው የግል፣
ፃፈልኝ ደብዳቤ እግዜር።
እኔም በፖስጣ፣
  የግል ብዬ አትሜ፣
መልሴን ላኩለት ፅፌ።

# እንደ ነፃነት ያሉ ቃሎች

ቃሎች እንደነፃነት ያሉ፣
ግሩም፣ ካፍ ሲወጡ የሚጥሙ፣
ነፃነት፣ ካውታሩ ላይ ከልቤ፣
ያዜማል ሙሉ ቀን፣
        ያዜማል ሁል ጊዜ።

ቃሎች እንደ አርነት ያሉ፣
ሊያስለቅሱኝ የሚከጅሉ።
እኔ 'ማውቀውን ብታውቁ፣
በገባችሁ ምክንያቱ።

# አረንጉዋዴ ትዝታ

መልካም ጊዜ ነበር ጦርነቱ፣
ገንዘብ ወደቤት መግባቱ፣
ደም መፍሰሱ፣ ደም መውጣቱ፣
ሩቅ ነበርና ካለንበት፣
          ደም፣
ግን ቅርብ፣ ገንዘብ፡፡

# ሀዘን

አይኖች
ማልቀስ አቅቶአቸው
ሲፈዙ፡፡

ልብም
አምዋምዋትን
አለማወቁ፡፡

# ስልቾታ

ዛሬም እንደትናንት፣
ነገም እንደዛሬ፣
ጠብ! ጠብ! ጠብ! ጠብታ፣
የስልቾታ፡፡
እያለቀ ነው ህይወቴ፣
ዛሬም እንደትናንት፣
ነገም እንደዛሬ፡፡

# ትካቴ

አቤት፣
መታከቴ፣
ሁሌ፣
ድህነቴ፡፡

# ያገር ናፍቆት ትዝታ

የባቡሩ ድልድይ፣
የሀዘን ዜማ ነው የተንጠለጠለ ባየር፣
የባቡሩ ድልድይ፣
የሀዘን ዜማ ነው የተንጠለጠለ ባየር፣
ያስናኛል መሄድ፣ መኮብለል፣
ባቡሩ ባለፈ ቁጥር፣

ባቡር ጣቢያ ሄድኩ፣
ልቤ ባፌ ሞልቶ፣
ባቡር ጣቢያ ሄድኩ፣
ልቤ ባፌ ሞልቶ፣
ልመለከት ፉርጎ፣ልፈልግ ልፈልግ፣
ይዞኝ ወደ ደቡብ የሚወርድ የሚነጉድ።

የሀገር ቤት ናፍቆት፣ ምንኛ ነው ከባድ፣
ላለማልቀስ ብዬ፣ እስቃለሁ በግድ።

# የካራቢያን ፀሀይ ጥልቀት

እግዜር እየደማ ነው፣
        እየተንሰራፋ ደሙ ከሰማይ፣
እያቀለመው ጥቁሩን ባህር፣
        እየለወጠው ወደቀይ፣
እንዲያ ነው ከካራቢያን፣
ፀሀይ ስትጠልቅ ስትዳፈን።

# ኩ ክላክስ

ወሰዱኝና ወደውጭ፣
ገለል ወዳለ ቦታ ጭር፣
«ታምናለህ ወይ» አሉኝ፣
«በታላቁ የነጭ ዘር፤»
እኔም፣ «ጌቶቼ» አልኩ፣
«እውነቱን ለመናገር፣
የምትለቁኝ ከሆነ፣
አምናለሁ በሆነው ነገር፤»

«አንተ ልጅ» አለ፣ ነጩ ሰውዬ፣
«እንዲህ ከፊቴ ቆመህ፣
መቀለድህ ነው በኔ፤»
ጭንቅላቴን መቱኝ፣
ጣሉኝ፤
ወድቄም ደበደቡኝ፣
ክላኑም፣ «አንት ባርያ» አለኝ፣
«ተመልከትና አይኔን፣
በታላቁ የነጭ ዘር፣
ንገረኝ እንደምታምን።»

# የመጨረሻው ኩርባ

ኩርባውን ስትል እጥፍ፣
ከራስህ ጋር ስትገናኝ፣
ግጥም ስትል ከፊትህ፣
ይገባህል ያኔ፣
የቀሩህን ኩርባዎች፣
እንደጨረስክ ታጥፈህ።

# ጨቅላ

አልበርት!
አንተን እኮ ነው፤ አልበርት!
ኸመንገድ ውስጥ አትጫወት፡፡
ታያቸው የለ መኺኖቹ፣
ሲያልፉ፤
ሞተህ ታርፈዋለህ፣
ይጨፈልቅህና አንዱ፡፡
አልበርት!
ኸመንገድ ውስጥ አትጫወት፡፡

# ማማ

ማማ ነው፣ ሞት፣
ነፍስ አርጋ 'ምትወጣበት፣
በጥሞና ልታሳልፍ አንድ ሰአት፣
ለዘለአለም አለም የማያልቅ፣ የማያከት፡፡

# እኔና ዝማሬዬ

ጥቁር፣
እንደ ገራሙ ጨለማ፣
ጥቁር፣
እንደ ልዝቡ የዋህ ሌሊት፣
ጥቁር፣
እንደ ጥልቁ ለም መሬት፣
ሰውነት፣
ከአፍሪቃ የወጣ፣
ጥቁርና ጠንካራ፣
እንደመጀመሪያው የብረት ቅላጭ፣
ካፍሪቃ፤
ዜማም እንዲሁ ካፍሪቃ፣
እንደጥቁር አፈር፣
ያማረና የጎላ፤
ጠንካራ፣
እንደ ጥቁር ብረት፣
ርህሩህ፣
እንደ ጥቁር ሌሊት፣
የኔ ዜማ፣
ከጥቁሮቹ ከንፈሮች፣
ያፍሪቃ፣
ጥልቅ፣
እንደለም አፈር፣
ውብ፣
እንደድቅድቅ ጨለማ፣
ጠንካራ፣
እንደብረት አቦል፣
ጥቁር፣
ከአፍሪቃ፣
እኔና፣
የኔ ዜማ።

## ነፃነት - ፩

ነፃነት አይገኝም፣
  ዛሬም ሆነ ዘንድሮ፣
ወይም ለዘለአለም ጨርሶ፣
በድርድር በፍርሀት ከቶ።

እንደሌላው ሁሉ፣
  አለኝ መብት፣
ራሴን ችዬ ለመቆም፣
  ለመሆን ባለመሬት።

ሰለቸኝ መስማቱ፣
ያለው ላይቀር ሲሰኙ፣
ነገ ሌላ ቀን ነው ሲሉ።
አልፈልግም ነፃነት ለበድኔ፣
በህልም እንጀራ አልኖርምና እኔ።
  ጠንካራ ዘር ነው፣
    ነፃነት፣
  የተተከለ፣
   በሀያል ፍላጎት፣
  እኖራለሁና እኔም፣
   እፈልጋለሁ ነፃነት፣
  እንደናንተ።

## አስረዱኝ

ለምንድን ነው ብቸኝነቴ፣
ለምንድን ነው ዝማሬዬ፣
ለምንድን ነው ምኞቴ የኔ፣
    መሆኑ፣
በይደር የሚያዘው በረጅሙ?

# ጥቁር ሰራተኞች

ንቦች ይሰራሉ፣
ግን ፍሬውን ይነጠቃሉ፡፡
እኛም እንደንቦች ነን፣
አንቀርም ግን እንዲያ ሆነን፣
ለዘለአለም፡፡

# እግዜር

እግዜር ነኝ፣
የሌለኝ ዘመድ ጉዋደኛ፣
ማክተሚያ በሌለው አለሜ፣
የንፅህና ብቸኛ፡፡

ይመላለሳሉ በውብ ምድር፣
ወጣት ፍቅረኞች ከበታቼ፣
አልችልም እንዲያ መሆን፣
ወርጄ፣
አምላክ ነኝና፣
ከዙፋኔ፡፡

ፀደይ!
ህይወት ፍቅር ነው፣
ፍቅርም ህይወት፣
ይሻላል ሰው መሆኑ፣
ከብቸኛ አምላክነት፡፡

# ቀለም

ተጎናፅፈው፣
እንደበንዲራ፣
በኩራት፣
እንደቡትቶ ሳይሆን፣
በሀፍረት፡፡

ተጎናፅፈው እንደዝማሬ፣
እንደሚያስተጋባ ድምፁ፣
ይቅርና ማላዘኑ፣
ይቅርና ማልቀሱ፡፡

# ደሴት

አንተ የሀዘን ማእበል፣
እባክህ አሁን አታስምጠኝ፤
እንዴት እንደሆነ ባልገልፀውም፣
ደሴቱ ከፊቴ እየታየኝ፤
እየዋለሁ ደሴቱን፣
ካማረ አሸዋው ጭምር፤
አንተ የሀዘን ማእበል፣
እባክህ አድርሰኝ ከዳር፡፡

# ፍፃሜ

ሰአቶች የሉም፣ ከግድግዳው፣
ጊዜም የለ፣ ከናካቴው፣
ጎህ ሲቀድ፣ ፀሀይ እስክትጠልቅ፣
የሚገዋዝ ጥላ የለም፣
ወለሉን የሚያቋዋርጥ፣
ከበራፍ ውጭ፣ ብርሀን የለም፣
ጨለማም፣
በራፍ የለም።

# ሰላም

መቃብራቸውን አለፍን፣
የወደቁትን ከዚያ፣
ድል አድራጊም ሆኑ፣ ተሸናፊ፣
የላቸውም ደንታ።

አይታያቸው፣
ከመቃብር ጨለማ፣
ማን እንዳሸነፈ፣
ድሉን እንደመታ።

# ርኩስ

የሚያሳብደኝ እኔን፣
አይነካሽም አንችን፡፡
አይቀር እንደሁ መሞከሬ፣
አንችም እስክትከንፊ እንደኔ፡፡

# ወጣት መርከበኛ

ሀይሉ ነው የራሱ፣
ሳቁም ነው የግሉ፣
ዛሬም ነው የራሱ፣
ከሞት ባሻገር ያለውም ጊዜ ንብረቱ-
ጠንካራው ወጣት መርከበኛ፣
የሰፊው ባህር መንገደኛ፡፡

ገንዘብ ለምንድን ነው?
ለማጥፋት፣ ይላል፡፡
ጠጅስ?
ለመጠጣት፡፡
ሴትስ?
ለፍቅር፡፡
ዛሬስ?
ለጨዋታ፣ ለመጨፈር፡፡
አረንጉዋዴው ባህር፣
 ለብርታት፣

ጥቁሩ አፈር ደግሞ፣
 ለፈገግታ፡፡
ምንም የለም፣ ከምናዬው የተለዬ፣
 ካለንበት ህይወት ሌላ፡፡

# ማደሪያ ቤት

ከማደሪያ ቤቶች ሁሉ፣
መቃብር ነው ርካሹ፣
እንግዲህ ከቀናት ባንዱ፣
አይቀርልንም ከዚያ ማደሩ፡፡

ሀብታምና ደሀ፣
የሚካፈሉት በእኩልነት፣
መቃብር ነው እርካሹ፣
መኖሪያ፣ ማደሪያ ቤት፡፡

እኔ ግን አልደርስ ከዚያ፣
መቆዬት ከቻልኩ ካለሁበት፣
ይሁን ብያለሁ መቃብር፣
እርካሹ ማደሪያ ቤት፡፡

# ወጣት ሽርሙጣ

የጥቁር ዳማ ፊትዋ፣
የጠወለገ አበባ ነው፣
እንደተሰበረ አገዳው፤
እንዲያ አይነቶቹ ከሀርለም፣
ይላሉ ርካሽ ናቸው፡፡

# የአፍሪቃ-አሜሪካዊ ስባሪ

እጅግ ቆይታ፣
እጅግም 'ርቃ፣
ትኖራለች አፍሪቃ፣
ሳትተው ማስታወሻ፣
የሚሆን ለትካዜ፣ ለትዝታ፣
ከሚፈጥሩት በቀር፣ የታሪክ መፅሀፎች፣
ወይም እነዚያ ዘፈኖች፣
በምታቸው ከደማችን ያዋሀዱት፣
በምታቸው ከደማችን ያፈለቁት፣
የሀዘን እንጉርጉሮ፣
በእንግዳ ቃላት፣ ባልሆነ ልሳን የኔግሮ፡፡
እጅግ ቆይታ፣
እጅግም 'ርቃ፣
እንዲህ አለች አፍሪቃ፣

ጊዜ አልፎበት ታፍኖ፣
ከበሮው ሲመታ እንዲያም ሆኖ፣
ይህ የጥንታዊ ምድር እንጉርጉሮ፣
ምኞቱ የተቀጨበት፣
ያለሀገር የቀረ ህዝብ መሪር ለቅሶ፣
ይሰማኛል ዜማው፣
በታላቅ የዘር ጭጋግ ውስጥ አልፎ፣
እጅግ ቆይታ፣
እንዲሁም 'ርቃ፣
ይታየኛል ጥቁር ፊትዋ፣ ያፍሪቃ፡፡

# ዱር አዳሪ

ተስፋ የቆረጥን፣
ግድ የሌለን፣
የራበን፣
የሌለን 'ምንበላበት፣
የሌለን 'ምንተኛበት፣
የደከመን፣
ማልቀስ እንኳ የተሳነን፡፡

# ባዶ ቤት

በባዶው ቤት ነበር፣
የመጣሁት ልኖር፣
ግን ከባዶው ቤት ውስጥ፣
አገኘሁ ባዶ ሲኦል፡፡

ለምንድን ነው ባዶ ቤት፣
ያልነካው የሰው ስቃይ፣
የሚይዘው ሰቀቀን፣
ሰፊው አለም ከሚችለው በላይ፣
ህመሙ፣ ያዘለው፣
ከስል ካራ የሚያይለው፣
ለምንድን ነው?